# ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋህዶ

## ወርኀ ጥቅምት (ዘመነ ጽጌ) ሦስተኛ ሳምንት

### የዕለቱ ምስባክ

ጻድቅሰ ከመ በቀልት ያፈሪ
ወይበዝህ ከመ ዝግባ ዘሊባኖስ
ትኩላን እሙንቱ ውስተ ቤተ
እግዚአብሔር

ጻድቅ ግን እንደ ዝግባ ያፈራል
እንደ ሊባኖስ ዝግባም ያፈራል
በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ተተክለዋል

መዝ ፺፩፥፲፪

ወንጌል፥ ማቴ ፲፪፥፩-፳፪
ቅዳሴ፥ ጐሥዐ (ቅዳሴ ማርያም)

### የዕለቱ ትምህርት

# እንደ አንተ ያለ መሃሪ ማን ነው?

ቅዱስ ያሬድ የመዝሙሩ አዝማች ያደረገው ወመኑ መሃሪ ዘከማከ (እንዳንተ ያለ መሃሪ ማነው?) የሚለውን የምስጋና ቃል ነው። ምክንያቱም ሲገልጽ ከኖኅ ጋር ኪዳንን ያጸናህ እንዳንተ ያለ መሃሪ ምነው? ለእስራኤል መናን ያወረድክ እንደአንተ ያለ መሃሪ ማነው? ምድርን በጽጌያት ያስጌጥክ እንደ አንተ ያለ መሃሪ ማነው? ሰማይን ምድርን የፈጠርክ ፀሐይን ጨረቃን ያዘጋጀህ እንደ አንተ ያለ መሃሪ ማነው? ሁሉም በአንተ ተስፋ ያደርጋልና ይላል። ሊቁ ቅዱስ ያሬድ በብሉይ ኪዳን የተገለጸውን የእግዚአብሔርን ምህረት ርኅራኄ ስለሚያውቅ ነው ይህን መዝሙር ያዘጋጀው።

ይህን መዝሙረ ያሬድ ከተነበበው መልእክት ፩ኛ ቆሮንቶስ ፲፥፩-፲፱ እና በማቴዎስ ፲፪፥፯ ጋር ያዛምዱ።

## የእግዚአብሔር ምሕረት በመጽሐፍ ቅዱስ

ምሕረት ማለት ቅጣት ለሚገባው ወንጀለኛ ይቅርታ ርኅራኄ ማድረግ ማለት ነው። (መዝ ፶፥፩ ። መዝ ፶፥፯-፳) ለባልንጀራ ለድሃ ምሕረት ስናደርግ እግዚአብሔርን እናከብራለን (ምሳ ፲፬፥፳፩ እና ፴፩ ። ሆሴ ፲፬፥፫)።

የእግዚአብሔር ልጅ ስለ እኛ በመስቀል ላይ በመሞት ለበደለኞች ታላቅ ምሕረት አደረገልን (ኤፌ ፪፥፬-፭ ። ፩ኛ ጴጥ ፩፥፫ ። ሮሜ ፭፥፮-፲) እግዚአብሔር አምላካችን ከመስዋእት የበለጠ ምሕረትን እንደሚወድ በነቢያት ተገልጿአል። ዛሬ የተነበበውም ወንጌል የሚያስገነዝበንም ይህንኑ ነው። የእግዚአብሔርን ምሕረት በብሉይ ኪዳን ስናይ እጅግ የበዛ (ዘኍ ፲፬፥፲፰)፤ እስከ ሰማይ ደመናት የሚደርስ (መዝ ፶፮፥፭)። እንደ ሰማይ የረዘመ (መዝ ፩፻፲፫፥፲፩)፤ የተትረፈረፈ እና የበዛ (መዝ ፶፮፥፯)፤ ቃሉን በሚፈሩት ላይ እስከ ሺህ ትውልድ የሚያጸና (ዘፀ ፴፬፥፯)፤ ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም የሚኖር (መዝ ፩፻፲፫፥፲፯ ። ፩፻፴፮ በሙሉ) ነው።

በብሉይ ኪዳን ላይ እንደተመለከትነው በብዙ ቦታ የእግዚአብሔር ምሕረት ተጠቅሷል። በሐዲስ ኪዳን ደግሞ በመስቀል ላይ በዋለው በልጁ ተገልጧል። ብሉይ ኪዳን በብዙ ገፅ ላይ አንድ ቀን የታየው የኢየሱስ ክርስቶስ ምሕረት ትርጉም የሰፋ ነው።

እንግዲያውስ እንደ ሎጥ ከእሳት ነጥቆ ያወጣንን የጌታን ምሕረት እናስብ (ዘፍ ፲፱፥፲፱) እንደ ያዕቆብም ከተደረገልን ምሕረት ርኅራኄ የተነሣ ሳይበጋኝ ምሕረት በዛልኝ እንበል (ዘፍ ፴፪፥፲) እንደ አብርሃም አሽከር የእግዚአብሔር ምሕረት ስለሚያደርግልን እንለምን (ዘፍ ፴፬፥፲፪)።

እንደ ያዕቆብ ስለተደረገልን ምሕረትም እግዚአብሔርን እናመስግን (ዘፍ ፳፬፥፳፯) እንደ ኑኃሚን እግዚአብሔር ተኣምራዊ በሆነ መንገድ ስለሚያደርገው ሕይታዊ መስተካከል እግዚአብሔርን እናመስግን (ሩት ፪፥፳) የእግዚአብሔር ምሕረት የዕውሮች ጩኸት ትሰማለች ዕውራንን ታበራለች (ማር ፲፥፵፮-፶፪)።

## የዕለቱ የቅዱስ ያሬድ መዝሙር ርዕስ

ዘመነ ጽጌ፣ ከመስከረም ፳፮ እስከ ህዳር ፭ ቀን ድረስ ያለው ዘመነ ጽጌ ይባላል። በዘመነ ጽጌ በሙሽራውና በሙሽራይቱ ምሳሌ ክርስቶስና ቤተ ክርስቲያኑ በጽጌ (በአበባ) መነጋገራቸውን መኃልየ መኃልይ የተዘመረ ይታሰብበታል። እንዲሁም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሕጻኑን ኢየሱስን ይዛ ወደ ግብጽ መሰደዷን፣ በስደትም ከሕጻኑ ጋር ብዙ መከራ መቀበሏን በሕጻኑም ስደት የግብጽ ጣዖታት መሻራቸውን፣ ሰይጣንም ከሰው ልቡና መሰደዱን፣ ክርስቶስም ተስፋ ስዱዳን መሆኑን «ኢየሱስ ስዱድ ተስፋሆሙ ለስዱዳን» እያለች በመዘመር ታሳስባለች።

ወመኑ መሃሪ ዘከማከ
(እንዳንተ ያለ መሃሪ ማን ነው)

### በቅዳሴ ሰዓት የሚነበቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች

| | ንባብ | አንባቢ |
|---|---|---|
| 1 | ፩ኛ ቆሮ ፲፥፩-፲፱ | ዲያቆን (ገባሬ ሰናዩ) |
| 2 | ራዕ ፲፬፥፩-፮ | ዲያቆን (ንፍቅ ዲ.) |
| 3 | የሐዋ ሥራ ፬፥፲፱-፴፩ | ረዳቱ ቄስ (ንፍቅ ካህን) |

## የቅዳሴ ጥቅስ

አዘከሪ ምሕረተ ወአኮ መዓተ
ምሕረትከ ይተለወኒ በኵሉ መዋዕለ ሕይወትየ

መዓትን ያይደለ ምትረትን አሳስቢ
ምሕረትህ በሕይወት በዘመኔ ሁሉ ይከተለኛ
መዝ ፳፪፥፮

ኢትዝክር ብነ አበሳነ ፍጡነ ይርከበነ ሣህልከ እግዚአ ዘትካት
የቀደመ በደላችን አታስብብን
አቤቱ ይቅርታህ ፈጥኖ ይደረግልን
*(የኤጴፋንዮስ ቅዳሴ)*